# እኔን እኔ በላው!

ጥርሴ ጥርሴን ፈጨው፣ ምላሴን አኘከው፣
እጄም እጄን ቆርጦ ደም ብቻ አደረገው፣
እግሬም እግሬን ጠልፎ መሬት ደባለቀው፣
አፌ አፌን አፈነው፣ እስትንፋሴም ነሳው፣
እጣቴም ተነስቶ አይኔን ጠነቆለው፣
ራሴ በትዛዝ እኔን በኔ አስበላው።

ራስ ከግሬ ቀድሞ ነገር እየሰራ፣
እጆቹ በእግሮቹ እንዲያሴሩ ሴራ፣
እንዲተራረዱ በተራ በተራ፣
ያቀብላቸዋል መክተፊያውን ካራ።

እኔን ለማረጃ ይሰጠኛል ካራ።
ከመቆም መውደቅን የመረጠልኝን፣
ደረቴን በእጆቹ የሚያስደልቀኝን፣
አካሌን በጥፍሬ የሚያስቧጭረኝን፣
እራሴን ቁረጡት ለኔ ያልሆነኝን።

ነፍሴን ከነፍሴ ጋር ከሚያፈታትነው፤
አካሌን በአካሌ ከሚያስቆራርጠው
ራሱ ይቅርብኝ አንገቴም ይቅለለው።

ኧረ እሪ በሉ! እኔን እኔ በላው፣
እራሴ ላናቱ ባርኔጣ ባማረው፣
ግራን እጇ ለቀኙ ባእድ ነው እያለው፣
አካሌን ባካሌ እኔን በኔ አስበላው።

መስፍን በየነ መድሃኔ
May 2007